MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION
Achievement Matters Most

ናንሲ ኤስ ግራዝሚክ — ማርቲን ኦማሊ
የስቴቱ ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ — አገረ ገዢ

Maryland State Department of Education
Division of Special Education/Early Intervention Services
200 W. Baltimore Street, Baltimore, MD 21201
www.marylandpublicschools.org

# የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል
# የልዩ ትምህርት የስቴት አቤቱታ መፍቻ ሥርዓቶች

# ክፍል B

## I. ሥልጣን

ሀ/ 34 CFR §300.151 *et seq.*

ለ/ COMAR 13A.05.01.15A

## II. ዓላማ

ሀ/ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል (MSDE) በአካለስንኩላን ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌና (IDEA) በተያያዙት የፌዴራል እና የስቴት ሕጎችና ደንቦች መሠረት የሚከተሉትን የአቤቱታ ማጣሪያ ሥርዓቶች ይይዛል። MSDE በአንቀጽ 34 CFR §300.153 ውስጥ የተጠቀሱትን አስፈላጊ ነጥቦች የሚያሟሉና በእነዚህ ሥርዓቶች መሠረት MSDE ጋር የገቡ አቤቱታዎችን በሙሉ የመፍታት ኃላፊነት አለበት።

ለ/ በአንድ አቤቱታ ምርመራ ምክንያት የታዘዙ የማረሚያ ድርጊቶች መፈጸማቸውን መከታተል፣ እንዲሁም የማረሚያ ድርጊቶች እንዲፈጸሙ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣ ሙያዊ እርዳታ መስጠትና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ የMSDE ኃላፊነት ነው።

## III. የአቤቱታ መስፈርቶች

ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ፣ ከአሁን በኋላ "አቤቱተኛ/ኞች" ተብሎ የሚጠራው፣ ከሜሪላንድ ስቴት ውጪ የሆኑትንም ጨምሮ፣ MSDE ጋር አቤቱታ ማስገባት ይችላል። አቤቱታው ከዚህ በታች የሚገኙትን መስፈርቶች በሙሉ እስካሟላ ድረስ፣ MSDE ከሌሎች በ MSDE ውስጥ ከሚገኙ ክፍሎች ወይም ከስቴት ወይም ከፌዴራል መንግሥት የመጡ አቤቱታዎችን ይፈታል።

ሀ. አቤቱተኛው MSDE ዌብሳይት ላይ በ www.marylandpublicschools.org አድራሻ (የ Division of Special Education/Early Intervention Services ገጽ ላይ ሄደው ከዛ የ Complaint Investigation and Due Process Branch

ገጽ ላይ ይሂዱ) የሚገኘውን የስቴት አቤቱታ ፎርም መጠቀም ይችላል ወይም በስልክ ቁጥር 410-767-7770 ሊደውልልን ይችላል። ይህንን ፎርም የመጠቀም ግዴታ ባይኖርም፣ አቤቱታው ፎርሙ ላይ የተጠየቀውን መረጃ በሙሉ፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች በሙሉ እንዳሟላ ሆኖ መያዝ አለበት።

ለ. አቤቱታው መጻፍ ያለበት ለረዳት ስቴት ተቆጣጣሪው በሚከተለው አድራሻ ነው Assistant State Superintendent, Division of Special Education/Early Intervention Services, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201።

ሐ. አቤቱታው MSDE ጋር በገባ ጊዜ ግልባጩ ለተማሪው የትምህርት መርሃ ግብር ኃላፊ ለሆነው የሕዝብ ድርጅት መላክ አለበት። አቤቱታው በልዩ ትምህርት ሥራ አስኪያጅ ስም ወይም በሌላ የመርሃ ግብሩ አስተዳዳሪ ስም ቢላክ ይመረጣል።

መ. አቤቱታው በጽሑፍ የቀረበ እና አቤቱታውን የሚያቀርበው ሰው የፈረመው መሆን አለበት። MSDE በፍጹም ትክክለኛ ቅጂ የመጡ፣ ከዚህ በታች በክፍል III አንቀጽ ሠ እስከ በ ያሉትን መስፈርቶች ያሟሉ አቤቱታዎችን ይፈታል።

ሠ. አቤቱታው የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

1. አንድ የሕዝብ ድርጅት የ IDEAን መስፈርት ደንብ የተላለፈ መሆኑን የሚናገር መግለጫ፣
2. መግለጫው የተመሠረተባቸውን ተጨባጭ ነገሮች (አቤቱተኛው ክሱን/ክሶቹን የሚደግፍ ማንኛውንም የሰነድ ግልባጭ አያይዞ እንዲያቀርብ ይበረታታል)፣
3. የአቤቱተኛው ፊርማና የመገናኛ መረጃ፣
4. ክሶቹ የተወሰነ ተማሪን የተመለከተ ከሆነ፣ አቤቱተኛው የሚከተሉትን መረጃዎች አብሮ ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ/ የተማሪውን ስምና የመኖሪያ አድራሻ፣

   ለ/ ተማሪው የሚሄድበትን ትምህርት ቤት ስም፣

   ሐ/ ተማሪው ቤት አልባ ከሆነ የተገኘውን ተማሪውን የመገናኛ መረጃና ተማሪው የሚሄድበትን የትምህርት ቤት ስም፣

   መ/የተማሪውን ችግር ባሕርይ መግለጫና ከችግሩ ጋር የተያያዙ ተጨባጭ ነገሮች፣ እና

ሠ/ አቤቱታው በገባበት ጊዜ በሚታወቀውና በተገኘው መረጃ ላይ ይተመሠረተ ለችግሩ መፍትሔ።

ረ. አቤቱታው የሚያቀርበው ክስ MSDE አቤቱታው ከደረሰው ቀን እስከ አንድ (1) ዓመት በፊት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተከሰተ መተላለፍ መሆን አለበት።

ሰ. የሕዝብ ድርጅቱ የ IDEAን የመስፈርት ደንብ እንደተላለፈ የሚናገረው መግለጫ የአንድን ልጅ የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ የትምህርት ምደባን ወይም ለልጁ የሚሆን የ ነጻ አግባቢነት ያለው ሕዝባዊ ትምህርት (FAPE) አቅርቦት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፣ እንዲሁም ማንኛውም ሌላ የሕዝብ ድርጅት የ IDEAንና የተያያዙ የፌዴራልና የስቴት ደንቦችን ስለተላለፈ ክስ ሊሆን ይችላል። ይህም የሕዝብ ድርጅቱ የፍትህ ሂደት ችሎት ላይ የተሰጠውን ፍርድ በተግባር ስላዋለ ክስ ማቅረብን ያካትታል። ስምምነቶችን፣ የግልግል ስምምነቶችንና በመፍትሔ ስብሰባ በኩል የተደረሰባቸው ስምምነቶች በማንኛውም በአውራጃው መሥራት የሚችል የአውራጃው የስቴት ፍርድ ቤት ወይም የዩናይትድ ስቴትስ አውራጃ ፍርድ ቤት ውስጥ በሕግ የሚከበሩ ስሆን፣ በአቤቱታ ሂደት በኩል ግን MSDE አይፈታቸውም።

ረ. አቤቱታው በክፍል III ውስጥ ከአንቀጽ ሀ እስከ በ የተገለጹትን መስፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ አቤቱታው በቂ አለመሆኑን MSDE ለአቤቱተኛው በጽሑፍ ያሳውቀውና እንዲሁም አቤቱታው የደንቦቹን መስፈርቶች እንዲያሟላ ምን ዓይነት ተጨማሪ መረጃ እንደሚያስፈልግና እነዚህን ሥርዓቶች አብሮ ያሳውቀዋል።

ሰ. አቤቱታው በአንድ ተማሪ ስም የገባ ከሆነና አቤቱተኛው የተማሪው ወላጅ ካልሆነ፣ MSDE ግኝቶቹንና ውሳኔዎቹን ማቅረብ እንዲችል ዘንድ አቤቱተኛው ወላጅ የፈረመው የፈቃድ መስጫ አብሮ ማስገባት አለበት። ፈቃድ መስጫው ወላጅ የፈረመውና MSDE ተማሪውን የተመለከተ መረጃ ለአቤቱተኛው አሳልፎ እንዲሰጥ ፈቃድ የሚሰጥ መግለጫ መሆን አለበት።

## IV. የአቤቱታ ምርመራ ሥርዓቶች

ሀ. አቤቱታው በደረሰ ጊዜ፣ MSDE በፍጹም ትክክለኛ ቅጂ አማካኝነት አቤቱታውን ለተጠሪው የሕዝብ ድርጅት ሠራተኛ ያስተላልፈዋል።.

ለ. አቤቱተኛውና የሕዝብ ድርጅቱ አቤቱታው እንደደረሰ የሚገልጽ፣ ምርመራ የሚደረግበትን ክስ/ሶች የሚያሳውቅ፣ ለመፍትሔ የሚኖረውን የጊዜ ሰሌዳ የሚነግር፣ ወገኖቹ ክሱን/ሶቹን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ የማስገባት መብት እንዳላቸው የሚገልጽና አቤቱታውን ለመፍታት የተመደበውን የMSDE ሠራተኛ የሚያሳውቅ ማስታወቂያ በጽሑፍ ይቀርብላቸዋል። የሕዝብ ድርጅቱ ለአቤቱተኛው የአቤቱታ ደብዳቤ ውስጥ የተገለጸውን መፍትሔ ለአቤቱተኛው ካቀረበ፣ የጽሑፍ ማስታወቂያው ይህንኑ የሚገልጽ መግለጫ የያዘ ይሆናል፣ MSDEም ጉዳዩ ተፈቷል ብሎ ይደመድማል።

አለመግባባቱን ወይ በግልግል ለማስኬድ በመስማማት ወይም ኦፊሲዬላዊ ባልሆኑ መንገዶች ለአቤቱታው በተቻለ መጠን በቶሎ መፍትሔ ለማግኘት እርምጃዎች እንዲወስዱ MSDE ወገኖቹን ያበረታታል።

ሐ. በትምህርት ዓመት ውስጥ የመጀመሪያው የጽሑፍ አቤቱታ እንደደረሰ፣ አቤቱታው የቀረበበት የሕዝብ ድርጅት የሥርዓታዊ መከላከያ ቅጂ ለአቤቱተኛው አስተላልፎ መስጠት አለበት።

መ. አቤቱታው የቀረበበት የሕዝብ ድርጅት ከተገቢው የትምህርት ሥርዓት ሠራተኛ ጋር ክሱን/ሶቹን አብሮ እንዲገመግም ይበረታታል። የትምህርት ሥርዓቱ ለክሱ/ሶቹ መልስ ከሰጠ፣ ለእያንዳንዱ የደንብ መተላለፍ ክስ ምላሽ መስጠት፣ የሕዝብ ድርጅቱ በወሰነው መሠረት ተጨባጭ ነገሮቹን ማቅረብና የደንብ መተላለፉ ተለይቶ ከታወቀ፣ የማረሚያ ድርጊቶች ማቅረብ ወይም ተማሪው አገልግሎትች ያጣበትን ለማረም የተወሰዱ የማረሚያ እርምጃዎችን መግለጽ አለበት። የደንብ መተላለፉ በተመሳሳይ ሁኔታ ያሉ ተማሪዎችን የነካ ከሆነ፣ የሕዝብ ድርጅቱ እነዚህ ተማሪዎች አገልግሎት ያጡበትን ለማረም የሚደረጉ ድርጊቶችን ማቅረብ አለበት።

ሠ. አቤቱታውን ለመፍታት ቦታው ላይ የሚደረግ ጉብኝት አስፈላጊ ነው ብሎ MSDE ከወሰነ፣ ቦታው ላይ የሚደረግ የግል ጉብኝት ያኪያሂዳል።

ረ. MSDE ለአቤቱተኛውና ለሕዝብ ድርጅቱ የሚከተሉትን የያዘ የጽሑፍ ውሳኔ (የግኝቶች ደብዳቤ) ይሰጣል፦

1. ምርመራ የተደረገበት ክስ/ሶችን መግለጫ፣

2. ለእያንዳንዱ ምርመራ የተደረገበት ክስ የተጨባጭ ነገር ግኝቶችና ውሳኔ፣ የስቴት ወይም የፌዴራል ሕግ እና/ወይም ደንቦች ተጥሰው ከሆነም ይህንኑ የሚገልጽ መግለጫ እና ውሳኔው የተደረገበትን ምክንያቶች፣

3. If MSDE የስቴት ወይም የፌዴራል ሕግ እና/ወይም ደንቦች ተጥሰዋል ብሎ ከወሰነ፣ የግኝቶች ደብዳቤው የሕዝብ ድርጅቱ የሚከተሉትን ለማድረግ ምን ዓይነት የእርማት ድርጊቶች መፈጸም እንዳለበት የያዘ ይሆናል፦

    ሀ. የአገልግሎቶች መከልከልን እንዴት ማረም እንደሚቻል፣ ተገቢ ከሆነ የገንዘብ ካሳ መስጠትን ወይም ሌላ ለተማሪው ተገቢ የሆነ የእርማት ድርጊት መፈጸምን ጨምሮ፣ እና

    ለ. አካለስንኩልነት ላለባቸው ተማሪዎች ሁሉ ወደፊት የሚሰጡ ተገቢ የአገልግሎቶች አቅርቦት፣

4. የእርማት ድርጊቶችን የመፈጸሚያ የጊዜ ገደቦች፣

5. የእርማት ድርጊቶቹ በሚፈጸሙበት ጊዜ የሙያ እርዳታ ቢያስፈልግ የሚገናኙት የ MSDE ሰው፣ እና

6. ወገኖቹ MSDE በሰጠው ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ፣ አቤቱታ የተደረገበትን ጉዳይ ለመፍታት የግልግል ጥያቄ ማቅረብ ወይም የፍትህ ሂደት አቤቱታ የማስገባት መብታቸው የተጠበቀ እንደሆነ የሚናገር መግለጫ።

ሰ. MSDE አቤቱታው በደረሰው በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ የግኝቶች ደብዳቤው ካልተሰጠ፣ እንደዘገየ ይቆጠራል። አንድን አቤቱታ በተመለከተ ከተለምዶው ውጪ የሆኑ ልዩ ሁኔታዎች ካሉ ወይም አቤቱተኛውና የሕዝብ ድርጅቱ ግልግል ወይም ሌላ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ለማድረግ ከተስማሙ የጊዜ ገደቡ ሊራዘም ይችላል። ጊዜ ማራዘም ካስፈለገ፣ አቤቱተኛውና የሕዝብ ድርጅቱ ይህ አስፈላጊ እንደሆነ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ከ MSDE ይላክላቸዋል።

ሸ. የግኝቶች ደብዳቤው ላይ በተሰጡት ውሳኔዎች አንደኛው ወገን የማይስማማ ከሆነ፣ ይህ ወገን በምርመራው ጊዜ ያልታየ ወይም ያልነበረ ተጨማሪ መረጃ የመስጠት መብት አለው። ይህ መረጃ የግኝቶች ደብዳቤ ላይ ከሚገኘው ቀን እስከ አስራ አምስት (15) ቀናት ጊዜ ድረስ ውስጥ መሰጠት አለበት። ተጨማሪው መረጃ የምርመራ ውጤት የሆኑትን ውሳኔዎቹ እንደገና ለማገናዘብ የሚያስወስን በቂ መረጃ መሆኑን MSDE ይወስናል። መረጃው በቂ መሆኑን ከወሰነ በኋላ፣ MSDE ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ለመከለስ እንደወሰነና የታዘዙ የእርማት ድርጊቶች ካሉም የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ለጊዜው በእንጥልጥል እንዲቆዩ ወገኖቹን በጽሑፍ ያሳውቃቸዋል።

## V. ከMSDE ስልጣን ውጪ የሆኑ አቤቱታዎች

ሀ. አቤቱታው በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በቀለም፣ በብሄር፣ በጋብቻ ሁኔታ ወይም ሌላ የአካል ወይም የአእምሮ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ የአድሎ ክሶችን የያዘ ከሆነ ወይም ከልዩ ትምህርት ሕግ ውጪ ሌሎች ደንቦችና ሕጎች የሚሸፍኑት ተግባር ከሆነ፣ MSDE ምርመራ ለማካሄድ ከ MSDE ስልጣን ውጪ የሆኑትን ክሶች ለወገኖቹ በጽሑፍ ያሳውቃቸዋል። በእነዚህ ክሶች ላይ ሕጋዊ መብት ያለው ድርጅት የሚታወቅ ከሆነ፣ ስሙንና አድራሻውን MSDE በእዚሁ ማስታወቂያ ውስጥ ለአቤቱተኛው ያሳውቀዋል።

ለ. MSDE በግልግል በኩል የተደረሰበት ስምምነት ወይም የመፍትሔ ስብሰባ በሥራ ላይ አለመዋሉን መሠረት የሚያደርጉ ክሶች አይመረምርም። ማንኛውም ይህን ዓይነት ክስ ለመፍታት በአውራጃው መሥራት የሚችል ፍርድ ቤት መግባት አለበት።

ሐ. የደረሰው አቤቱታ የፍትህ ሂደት ችሎት አካል ከሆነ ወይም ከያዛቸው ብዙ ክሶች ውስጥ አንዱ ወይም ብዙው የችሎት አካል ከሆነ፣ MSDE ችሎቱ እስከሚገባደድ ድረስ በችሎት ውስጥ ያለውን የፍትህ ሂደት ችሎት ወደ ጎን

ማስቀመጥ አለበት። ማንኛውም የፍትህ ሂደት ችሎት አቤቱታ አካል ያልሆነ አቤቱታው ውስጥ ያለ ክስ በ MSDE አቤቱታ ሥርዓቶች እና ተገቢ የጊዜ ገደቦች መሠረት ይፈታል። ክሶቹ ወደ ጎን እንደሚቀመጡ እና ካሉም፣ የትኞቹ ክሶች በአቤቱታ ሥርዓት እንደሚፈቱ ውሳኔ ሲያደርግ MSDE ወገኖቹን በጽሑፍ ያሳውቃቸዋል።

D. ከዚህ በፊት እነዚህኑ ወገኖች የሚመለከት የፍትህ ሂደት ችሎት ውስጥ ውሳኔ የተደረገበትን አቤቱታ በተመለከተ ከሆነ MSDE ጋር የገባው አቤቱታ እንደገና ክስ የተነሳው፣ የችሎቱ ፍርድ ወገኖቹን የሚያስገድድ ቃል ሲሆን፣ MSDEም ይህንኑ ለአቤቱቱኛውና ለሕዝብ ድርጅቱ ያሳውቃል።

## VI. የአቤቱታ መፍትሔ

አቤቱታው በአጥጋቢ ሁኔታ በግልግል ወይም በሌላ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ እንደተፈታ ወይም አቤቱተኛው መልሶ አውጥቶት እንደሆነ የሚገልጽ ማስታወቂያ በደረሰው ጊዜ፣ MSDE አቤቱታው እንደተፈታ አድርጎ ይቆጥረዋል። ይህም አንድ የሕዝብ ድርጅት ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ በአቤቱታ ደብዳቤ ውስጥ የሰጠውን መፍትሔ ለማቅረብ ፈቃደኛ ሲሆንን ጨምሮ ነው።

## VII. የማረጋገጫ እንቅስቃሴዎች/የአቤቱታ ቀጣይ ክትትል

MSDE የፌዴራል ወይም የስቴት ሕግ ወይም ደንብ ጥሰትን የሚገልጽ የግኝቶች ደብዳቤ በሰጠ ጊዜ፣ የሕዝብ ድርጅቱ የእርማት ድርጊቱ/ቶቹ መጠናቀቃቸውን ማረጋገጫ ሰነድ እንዲያቀርብ MSDE ይጠይቃል።

ሀ. ማንኛውም ወገን፣ የግኝቶች ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ፣ የሙያ እርዳታ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል። የሙያ እርዳታ ሲጠየቅ የእርማት ድርጊቶቹን መጠናቀቅ በማያዘገይ ሁኔታ ሆኖ በጊዜ መጠየቅ አለበት።

ለ. የመጨረሻ ውሳኔውን በሌሎች መንገዶች በተግባር ለማዋል የሕዝብ ድርጅቶች ከMSDE ጋር መዋዋል ይችላል።

ሐ. የ MSDE ሠራተኞች የተወሰዱትን እርምጃዎች አይቶ አስፈላጊ የሆኑትን ድርጊቶች ለመፈጸም አጥጋቢ መሆናቸውን ይወስናል።

1. የእርማት ድርጊቱን/ቶቹን ለማሟላት የተወሰዱት ደርጃዎች አጥጋቢ ከሆኑ፣ MSDE ለወገኖቹ በጽሑፍ የቀረበ ማስታወቂያ ይሰጥና አቤቱታውን ይዘጋዋል።

2. የሕዝብ ድርጅቱ የወሰዳቸው እርምጃዎች ችግሩን/ሮቹን በአጥጋቢ ሁኔታ የሚያርሙ ካልሆኑ፣ MSDE ከሕዝብ ድርጅቱ ጋር በቅርብ አብሮ በመሥራት የተወሰዱት እርምጃዎች ለምን የተፈለገውን ውጤት እንዳልሰጡ እና የተፈለጉትን ውጤቶች ለማግኘት ምን ተጨማሪ እቅዶች እንደሚያስፈልጉ ይወስናል።

3. የሕዝብ ድርጅቱ የእርማት ድርጊቱን/ቶቹን ለመፈጸም ተገቢውን ጥረቶች ካላደረገ፣ MSDE እነዚህ ሥርዓቶች በሚገልጹት መሠረት የሕግ ማስከበር እቀባዎች ምን እንደሚሆኑ የሚያስረዳ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጣል።

## VIII. በሕግ ማስከበር

አንድ የሕዝብ ድርጅት በግኝቶች ደብዳቤ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በእነዚህ ሥርዓቶች መሠረት ጊዜው ተራዝሞ እስከተሰጠው ቀን ድረስ የእርማት ድርጊቱን/ቶቹን ካልፈጸመ፣ MSDE በ አንቀጽ COMAR 15A.05.02.07 መሠረት የማስከበሪያ እርምጃዎችን ይጀምራል።

## IX. ለሕዝብ ለማሳወቅ የሚደረጉ ጥረቶች

ሀ. የሕዝብ ድርጅቶች የአቤቱታ ሥርዓቶች ለወላጆች፣ ለድጋፍ ሰጪዎችና ለትምህርት ቤት ሠራተኞች በግልጽ መነገራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፣ እንዲሁም የሥርዓት መከላከያዎች መሰጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

ለ. MSDE ለድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በሚደረጉ መግለጫዎች በኩል፣ በሕዝብ ድርጅት ሠራተኞች በኩልና በተጠየቀ ጊዜ በሌሎችም በኩል የአቤቱታ ሥርዓቶቹን ያሰራጫል። MSDE እነዚህ ሥርዓቶች ታዋቂ እንዲሆኑ ከድጋፍ ሰጪና ከወላጅ ድርጅቶች ጋር፣ ለምሳሌ እንደ ሜሪላንድ የአካለስንኩልነት ሕግ ማዕከል (Maryland Disability Law Center)፣ የሜሪላንድ የወላጆች ቦታ (Parents' Place of Maryland)፣ ሁሉንም ያካተተ የሜሪላንድ የትምህርት ሕብረት (Maryland Coalition for Inclusive Education)፣ የሜሪላንድ ማህበረሰባዊ ግልግል (Community Mediation Maryland) እና ARC/Maryland ጋር ትብብር ፈጥሯል። እነዚህ ሥርዓቶች በ MSDE ዌብሳይት ላይ እንዲወጡም MSDE ያረጋግጣል።

*የገንዘብ ድጋፍ የቀረበው በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ከ IDEA ክፍል B ችሮታ #HO27A070035A፣ የዩ ኤስ የትምህርት ክፍል፣ የልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮ በኩል ነው። በዚህ ውስጥ የተገለጹ አስተያየቶች የዩ ኤስ የትምህርት ክፍልን ወይም ማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትን ወክለው አይደለም እንደሱም መታየት የለባቸውም። የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከልዩ ትምህርት መርሀ ግብሮች ቢሮ፣ ከልዩ ትምህርትና መቋቋሚያ አገልግሎቶች ቢሮና ከዩ ኤስ የትምህርት ክፍል ነው። ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው እንዲጋሩት ይበረታታሉ ሆኖም ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል የልዩ ትምህርት ክፍል/ቅድመ አገልግሎቶች መምጣቱን እባክዎን ያስታውቁ።*

*የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ሥራ ቅጥርን ወይም በአንዳንድ የመርሀ-ግብር ተሳትፎዎችን በተመለከተ ተጸዕኖ ሊያሳድር የሚችል በነሳ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት አድሎ አያደርግም። የክፍሉን አመራር በተመለከተ ጥያቄዎች ካልዎት የእኩልነት ማረጋገጫና መፈጸሚያ ቅርንጫፉን (Equity Assurance and Compliance Branch) በስልክ ቁጥር (410)767-0433 በመደወል ወይም በፋክስ ቁጥር (410)767-0431 መገናኘት ይችላሉ። የአካል ጉድለት ያለባቸው አሜሪካዊያን (Americans with Disabilities Act (ADA)) በደነገገው መሠረት ይህ ሰነድ በተጠየቀ ጊዜ በአማራጭ አቀራረቦች ዝግጁ ሆኖ ይገኛል። የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የልዩ ትምህርት/ቅድመ ገላጋይ አገልግሎቶችን ክፍል በስልክ ቁጥር (410)767-0858 ወይም በፋክስ (410)333-1571 ይገናኙ።*